# አገር እንዴት ሰነበተች?

የካቲት20ቀን2014ዓም(27-02-2022)

በስዊድን የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ የስነጽሑፍ ክፍል በዬሳምንቱ ከእሁድ እስከ እሁድ ድረስ በኢትዮጵያ አገራችን የተከናወኑትን አበይት ጉዳዮች የምናቀርብበት አገር እንዴት ሰነበተች የዛሬው ስርጭታችን በሚከተሉት ላይ የሚያተኩር ይሆናል።

ከአለፈው እሁድ ስንነሳ በእለቱ ከተከናወኑት አብይት ጉዳዮች ውስጥ በአገር ውስጥ ብቻም ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ትልቅ ትኩረት የተሰጠው የአባይ ግድብ የምረቃ ስነስርዓትን የሚመለከት ነበር። እርግጥ ነው የዬዘመናቱ የኢትዮጵያ መሪዎች አስበውና ሲመኙት የቆዬው ይህ የአባይን ውሃ ገድቦ ለአገራዊ ልማት ለማዋል የነበረው ምኞታቸው በተግባር ማዬትን የመሰለ ትልቅ ቁም ነገር የለም።

የውጭ ጠላቶቻችን የመሪዎቹ ፍላጎትና እቅድ እንዳይሳካ ያልተቆጠበ ጥረት አድርገዋል፤አሁንም እያደረጉ ነው።በግብጽ ፊትአውራሪነት በምዕራባውያን የተቀናጀው የማደናቀፍ ሴራ ምንም እንኳን ለዘለቄታው ከሽፈ ባይባልም ከዚህ ደረጃ ላይ መድረሱ የኢትዮጵያውያንን አልበገሬነት ማሳያ ነው።ይህ ማለት ግን የተደቀነው ችግር ተወገደ፣ አለቀ ደቀቀ ማለት አይደለም፤ገና ብዙ በግድቡ ዙሪያ የሚሽከረከር ፈተና አለ።የወደፊቱ ተግዳሮት ብዙ ናቸው።ዋናዋናዎቹም፣-

ግድቡ የተሠራበት አካባቢ ከጎሳ ፖለቲካው ጋር የሚኖረው ቁርኝት፣የግድቡ ተጠቃሚና ባለቤት ማን እንደሚሆን፣የግድቡ እቅድ ሙሉ ለሙሉ መሳካትና ሊገጥሙ የሚችሉ እንቅፋቶች ---ወዘተ ፈጠው የሚታዩ ፈተናዎች ናቸው።እያንዳንዱን ፈታ ፈታ አድርገን ብናዬው ፤-

ግድቡን ያስጀመረው በጸረ ኢትዮጵያዊነት ጥርሱን ነቅሎ ያደገው የወያኔው መሪ የነበረው መለስ ዜናዊ ሲሆን ፣ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይጠቅማል ብሎ ሳይሆን ትግራይን በመገንጠል አገር የመመስረት ዓላማውን ይዞ ከጎጃም ክ/ሃገር ገንጥሎ ቤኒሻንጉል ክልል ብሎ በፈጠረው ደካማ ከባቢ ማድረጉ ከባቢውን ጠቅልሎ በመያዝ የግድቡ ባለቤት ለመሆን ከነበረው ዓላማ ጋር የተያያዘ ነበር።ምንም እንኳን እሱ ቢሞትም ዓላማው አልሞተም።የትግራይ ተገንጣይ ቡድን አሁንም አገር በማተራመስ ከባቢውን ፋታ የነሳ ሲሆን ከታሪካዊ ጠላት ከሆነችው ግብጽ ጋር ግንባር ፈጥሮ ግድቡን ለመቆጣጠር አለያም ለማፍረስ እዬተንቀሳቀሰ ይገኛል።ለዚህም መሰል የከባቢ አማጽያንን በማደራጀትና በማስታጠቅ በጦርነት እንዲማገዱ አድርጓቸዋል። የጎሳ ስርዓቱ ጥቃቅን የጎሳ መኖሪያ ከባቢን አገር የመሆን መብት ስለሚፈቅድ ቤንሻንጉል የተባለው ክልል እራሱን ገንጥሎ ላለመሄዱ ዋስትና የለም።ከሄደም በመሬቱ ላይ ያለውን ሁሉ ይዞት ይሄዳል ማለት ነው።ይህ ከሆነ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዳር እስከዳር፣በውስጥም በውጭም ተባብሮ በገዛ ገንዘቡ የገነባውን ግድብ ይነጠቃል ማለት ነው። ይህ የነገ ስጋት ሲሆን በአሁኑ ወቅት ለአገር ኤኮኖሚ ይጠቅማል፣የጀርባ አጥንት ነው የተባለው ግድብ እራሱ የኤኮኖሚ ችግር ውስጥ ገብቶ እዬዳኸ ይገኛል።ሲጀመር በአምስት ዓመት ውስጥ በ80 ቢሊዮን ብር($5 ቢሊዮን ዶላር) ተጠናቆ፣ በአስራ ሶስት ተርባይን ከ6000 ሜጋዋት በላይ የኤሌክትሪክ ሃይል ያመነጫል፣ የተባለው አሁን ገና 70% ከሆነው ግንባታ ላይ በመድረስ የአንድ ተርባይን ጉልበት ከ375 ሜጋዋት የኤልክትሪክ ማመንጫነት አላለፈም።ከሳምንታት በፊትማ ሁለት ተርባይን 700ሜጋዋት አምርቶ ለሽያጭ ተሰራጭቷል የሚል ዜና ተነግሮ ነበር።ውሸት መስማት የለመደው ሕዝብ ያሉትን ተቀብሎ ከማጨብጨብ ይህንን ብላችሁን ነበር እኮ! ብሎ የመጠዬቅ ድፍረትም ሆነ ልማዱ የለውም።

ግድቡ አሁን ካለበት ደረጃ ላይ ለመድረስ ከ120 ቢሊዮን ብር በላይ ፈጅቷል ተብሏል።ከዚህ ውስጥ ከሕዝቡ በቦንድ ሽያጭ የተሰበሰበው ጠቅላላ ገንዘብ 11 ቢሊዮን ብር ብቻ መሆኑ ተገልጿል።ታዲያ 109 ቢሊዮኑ ብር ከዬት መጣ?ይህንን ከፍተኛ ገንዘብ ማን አዋጣ? ለምንና እንዴትስ ባለ ስምምነት? በሽያጭ፣ወይስ በሽርክና ወይስ በብድር፣ወይስ በእርዳታ?ብሎ መጠዬቅ ተገቢ ቢሆንም የደፈረ የለም። መቼም በአንድ ተቋም ላይ ከፍተኛ ድርሻና የመወሰን ሙብት የሚኖረው ከፍተኛ ገንዘብ ያወጣ ለመሆኑ አጠያያቂ አይደለም።ለቀጣዩስ የግንባታ ወጭ የሚያስፈልገው ገንዘብ ስንት ይሆናል? ከዬት ይመጣል?ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ መስጠት ተገቢ ነው።

ምንም እንኳን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጨለማ ይወጣል ተብሎ ቢነገርም በተግባር የሚታዬው ግን ለገበያ የሚቸበቸብ ሸቀጥ መሆኑ ነው።ሱዳን፣ኬንያ፣ጅቡቲ፣ኤርትራ---ወዘተ የግዥ ውል መፈራረማቸውና የስርጭት ማጠራቀሚያና ገመዱ እንደተዘረጋ ይፋ ሆኗል።የኢትዮጵያ ሕዝብ ተጠቅሞ የተረፈው ቢሸጥ ተገቢ ነው እንላለን፣ ግን ያ ሳይሆን ቅድሚያ ለገበያ መሆኑ ትክክል ስላልሆነ እንቃወማለን። ዱሮም ቢሆን እኮ ግብጾች ከኢትዮጵያ ሕዝብ ነጥቀው ለመጠቀም ነበር።የአሁኑ በሰላማዊ ሽያጭ ማጣት ካልሆነ በስተቀር ልዩነቱ ምንድን ነው? ያባይን ልጅ ውሃ ጠማው ይሏል ይኸ ነው። የሥራው መጓተት ከገንዘብ እጥረቱ በተጨማሪ ግብጾች የውሃ ክትረቱና የሃይል ማመንጫው ሂደት ቀስ በቀስ በ25ዓመታት መጠናቀቅ ይገባዋል ባዮች ናቸው።የኢትዮጵያ መንግሥት ከሦስት ዓመት በኋላ ይጠናቀቃል ቢልም ከመንግሥት ተደጋጋሚ ውሸቶችና ካለው ሁኔታ ስንነሳ በተባለው አጭር ጊዜ ውስጥ መጠናቀቁን እንድንጠራጠር ያደርገናል። የማጓተቱ ምስጢር የግብጾችን ፍላጎት የተቀበለና የተከተለ ያስመስለዋል።ለግድቡም ስኬት ሆነ ለሌላውም ብሔራዊ ጉዳይ ያገራችን ፣የኢትዮጵያ ህልውና ነው። ልዑላዊነቷና አንድነቷ ካልተከበረ ሁሉም ነገር የውሃ ላይ ኩበት ሆኖ ይቀራል። ለማንኛውም የተባለው ሦስት ዓመት ቅርብ ነው፤ሁሉንም የምናዬው ይሆናል።

ግራም ነፈሰ ቀኝ የአባይ ግድብ መገንባቱን የሚጠላ ኢትዮጵያዊ የለም ።ሆኖም ግን ከላይ የተጠቀሱት ጥያቄዎች መልስ ማግኘት አለባቸው እንላለን። ለዘለቄታው መፍትሔ ዋስትና የሚሆነው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊና የዜግነት የጋራ ሙብቱን ለማስከበር ጸረ ኢትዮጵያ የሆኑትን የውጭና የውስጥ ጣምራ ጠላቶቹን መክቶና የጎሳ ስርዓቱን ገርስሶ ያገሩና የሐብቱ ባለቤት ሊሆን የሚችልበትን አገር ወዳድ ስርዓት መመሥረቱ ብቻ ነው።

ወደ ቀጣዬ የሰሞኑ ገጠመኝ ስናመራ ከምስራቅ ወለጋ ሆረጉድሩ ከተባለው ቦታ ለዘመናት ከከባቢው ነዋሪ ጋር በጋብቻና በማህበራዊ ኑሮ እንዲሁም በቤተሰብ ሰንሰለት ተሳስረው፣ ወልደው ከብደው፣ ንብረት አፍርተው፣ ከፉና ደጉን ተካፍለው የኖሩ የአማራ ማህበረሰብ ተወላጆች በኦነግና በህወሃት ጥምር አሸባሪ ቡድኖች እንዲሁም በሥልጣን ላይ ባለው ኦህዴድ መራሹ ብልጽግና ቀጥተኛና ስውር ድጋፍ በሚካሄደው የዘር ማጥፋት ዘመቻ ሳቢያ የሞቱት ሞተው፣የቆሰሉት ቆስለው፣ንብረታቸውን ተነጥቀው በየአቅጣጫው ከተበተኑት መካከል መንግሥት ባለበት ከተማ ሌላው ቢቀር ሰላም እናገኛለን በማለት አዲስ አበባ ለመድረስ የቻሉት ከአራት መቶ በላይ የሆኑ ዜጎች ያጋጠማቸው ያልተጠበቀ ችግር ለሰሚው ይዘገንናል።እነዚህ መድረሻ ያጡት ዜጎች ፣ሕጻን፣ሽማግሌ፣ቁስለኛ፣ እርጉዝና አራስ በየመንገዱ ፈሰው ለርሃብና ችግር ተጋልጠው አይዟችሁ ብሎ ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆነው መንግሥት ነኝ ባይ የአሸባሪዎቹ አካል ይባስ ብሎ ከከተማዋ ለቀው እንዲወጡ አስገዳጅ ትዕዛዝ ከማሳለፉም በላይ በፖሊስ ሃይል እዬደበደበ በስቃይ ላይ ስቃይ አድርሶባቸዋል።የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላምና ጸጥታ ምክትል ሃላፊ የሆነችው ሊድያ ግርማ የተባለችው ጊዜ ያነሳት ተረኛ “ በእናንተ መክንያት ከተማችን እዬቆሸሸ ነው፤ከዚህ በኋላ አንድም ተፈናቃይ ወደ ከተማችን እንዳይገባ ጥብቅ ቁጥጥር እናደርጋለን” ባለችው መሠረት በካሚዎን አስጭና ደብረብርሃን አውላላ ሜዳ ላይ እንዲፈሱ ሆነዋል።የደብረ

ብርሃን አስተዳደርም ቦታና ባጀት የለኝም ብሎ መልሷቸዋል።የአዲስ አበባም አስተዳደር መልሶ አርሲ ጭኖ ልኳቸዋል፤የአርሲም አስተዳደር እንዲሁ ቦታና ባጀት የለኝም ብሎ ወደመጡበት መልሷቸዋል። በዚህ መንከራተት ላይ የደረሰላቸው የመንግሥትም ሆነ የተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲ የለም።በስሙ ሥልጣን ላይ ያሉትም ለምን ብለው መጠዬቅ ቀርቶ የእርዳታ እጃቸውን አልዘረጉላቸውም።በዚህ ስቃይ ላይ ከጎናቸው ቆሞ ስቃያቸውን ለማሰማት የሞከረው የባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲና የአዲስ አበባ ወጣትና ነዋሪ ሕዝብ ብቻ ናቸው።ነዋሪው ሕዝብ ካለችው እያካፈለ በቂም ባይሆን በህይወታቸው ውለው ማደር እንዲችሉ አድርጓቸዋል ።ጥያቄው ግን እስከመቼ በዚህ ሁኔታ ይዘለቃል የሚለው ነው። ይህንን ልዩ የሚያደርገው ግን በጎሳ ማንነታቸው ከኖሩበት ቦታ ተገደው መሰደዳቸው ብቻ ሳይሆን ያድነናል ብለው በተማመኑበት መንግሥት ቁሻሾች ተብለው ለስነልቦናዊ ቁስል ተዳርገው ካለምንም ማረፊያ መባረራቸው ነው።

ዜጋ በራሱ አገር ዋና ከተማ ቁሻሻ ነህ ተብሎ በካሚዎን ተጭኖ በማያውቀው ቦታ የፈሰሰበት ታሪክና አገር ተሰምቶም ታይቶም አይታወቅም።እርግጥ ነው ባለፉት ስርዓቶች በድርቅ ምክንያት ከአዲስ አበባ ከተማ ታፍሰው መጠለያ ውስጥ የገቡ መኖራቸው አይካድም።እነዚህም ወገኖች የዚያው ሰለባ ሆነው ከአርባ አምስት ዓመት በፊት ወደ ነበሩበት አካባቢ ተወስደው የሰፈሩ ቢሆኑም ኗሪው የፈራውን ደፍረው፣ ጫካ መንጥረው አልምተው፣አውሬና ወባ ሌላውንም በሽታ ተቋቁመው፣ ከራሳቸው አልፈው ለከባቢው ሕዝብ የተረፉ፣ሥራ ያስተማሩ፣ ጠንካራ የአማራ ገበሬዎች ናቸው።ከቶም ቢሆን የሌላውን መብትና ሃብት ያልነኩ፣በባህልና በእምነት የታነጹ ጨዋዎች፣የሌላውን ባሕልና ቋንቋ አክብረውና ተቀብለው ያደሩ እንጂ እንደሌላው ጎሳ ተወላጅ አሸባሪ ቡድን የሌላውን ከባቢ እዬወረሩ የሚዘርፉ፣ ማንነቱን የተጋፉና የነጠቁ አይደሉም።የነሱ ጥፋትና ወንጀል የሆነባቸው አማራ፣ኦርቶዶክስ ተዋህዶና የእስልምና እምነት ተከታይ ኢትዮጵያዊ መሆናቸው ብቻ ነው። የሰው ልጅ በማንነቱ፣ በእምነቱና በጾታው የሚገደል፣የሚደፈርና የሚፈናቀል ከሆነ ደግሞ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈጽሞበታል ማለት ነው።ይህንን ወንጀል ለሰብአዊ መብት ቆሚያለሁ ወይም ነግ በኔ የሚል ሁሉ ሊታገለውና ሊያወግዘው ብሎም ሊያሶግደው ይገባል።ለሥርዓቱ ያደሩና ፣የአማራው መሪና ተወካይ ነን የሚሉ ጥቂት ሰዎች የሚፈጸመውን የዘር ማጥፋት ወንጀል በማሳነስ ግጭት በሚል ስያሜ ወንጀለኞችን ተጠያቂ ላለማድረግ ይሞክራሉ።ይህ መጠነ ሰፊ የሆነው የተቀናጀ ጭፍጨፋ ኢትዮጵያን የማፍረስ አድማ አካል መሆኑን መረዳትና በአንድነት መቆም ነገ በሁሉም ላይ ሊደርስ ከሚችለው አስከፊ አደጋ ያድናል።

እንደ ኳስ ከየአካባቢው የሚለጉት ወገኖቻችን ላይ የሚደረገው ወከባ ቆሞ ለዘለቄታው ክብራቸውና መብታቸው ተጠብቆ የሚኖሩበት ቦታ ይሰጣቸው እንላለን።ለወደመባቸው ንብረት፣ብስቁልና፣ለጠፋው ህይወትና የመቁሰል አደጋ ካሳ እንዲሰጣቸውና ወንጀሉን የፈጸሙና ያስፈጸሙትም በሕግ ይጠዬቁ እንላለን።

የሰሞኑ ትልቁ አነጋጋሪ ማክሰኞ የካቲት 15 ቀን ወይም በፈረንጆች በፌብሩዋሪ 22 ቀን የተካሄደው የፓርላማ አስቸኳይ ስብሰባን የተመለከተው ነው።የስብሰባው ምክንያት የስድስት ወር የመንግሥት የሥራ ግምገማ ለማቅረብ ነው ቢባልም ፣ከፓርላማ አባላቱ የተመረጡ ሰዎች ላቀረቡት ጥያቄም መልስ ለመስጠት ነው ተብሏል።ከግማሽ ቀን ባላነሰ ጊዜ በነበረው የፓርላማ ቆይታው አብይ አህመድ መልስ ሰጠ ከሚለው ይልቅ እንደልማዱ ድራማ ሰርቶ አስጨብጭቦ የሄደበት ስብሰባ ነው ማለቱ ሳይሻል አይቀርም። ከስብሰባው ከአስር ቀናት በፊት የተወሰኑ የፓርላማ አባላት ተመርጠው ጥያቄ እንዲያቀርቡ ተደርጎ እንደነበር ከጠያቂዎቹ በኩል የተሰጠው መግለጫ ያመለክታል።በስብሰባው ላይ የውጭ አገርና የአገር ውስጥ ታዛቢዎች የነበሩ ሲሆን የጠ/ ሚኒስትሩ ማብራሪያ የመንግሥቱን ጥንካሬ፣

የኤኮኖሚውን እድገት፣ከሌሎች አገራት ፍላጎት ጋር የሚጣጣም ፖሊሲን በመከተል ያመጣውን መሻሻል በማጉላት፣የስብሰባውን ሶስት ሩብ ሰዓት የወሰደ ገለጻ ነበር።

እርስ በርሱ በሚቃረነው ንግግሩ የአገሪቱ ገቢ ጨምሯል ኤኮኖሚው አድጓል ያለው ከአድማጩ ጆሮ ሳይጠፋ ቀጠል አድርጎ ለውጭ ገበያው የሚቀርበው ምርት ማነስና ከውጭ የሚገባው ሸቀጥ መጨመር የገባያ ሚዛኑ አለመጣጣም ኤኮኖሚውን እንደጎዳና የዋጋ ግሽበት እንዳመጣ ይናገራል። ይህንን ብሎ ሳይጨርስ ለዋጋ ግሽበቱ ሸቃጩ ከተጠቃሚው ደብቆ አቅርቦቱን በመቀነሱ ነው ይልና ሸማቹም ዋጋ ከመቀጠሉ በፊት ይኑረኝ ብሎ በተጠዬቀው ዋጋ ለመግዛት ይረባረባል ፣ወይም ይቀንስ ይሆናል ብሎ ከመግዛት ይቆጠብና ገንዘቡን ያስራል ---ወዘተ በማለት እርስ በራሱ የሚጋጭ፣መያዣ መጨበጫ የሌለው ፣በሳይንሱ ያልተደገፈ የኤኮኖሚ ትንተናውን አዥጎድጉዶታል።በዚያም ብቻ አላቆመም፣ ለግሽበቱ ምክንያት የሆነው የሕዝቡ ብዛት ነው በማለት የወሊድ ቁጥሩን ለመቀነስ ልዩ ልዩ መንገዶች ተጠቀሙ ሲል የጃይናኮሎጂስት ወይም የማህበረሰብ ጠቢባን ተቋም የሆነውን የቤተሰብ መምሪያ ምክሩን በፌዝ መልክ እዬሳቀ ለፓርላማ አባላቱ ለግሷቸዋል።እርግጥ ነው ከምርት ጋር ያልተጣጣመ የሕዝብ ብዛት ለችግርና ለዋጋ ግሽበት ማጋለጡ አይካድም።መስተካከልም ይኖርበታል። ለምሳሌም ከዓመታት በፊት የቻይና ሕዝብ ከቢሊዮን በላይ ሲሆን፣የመመገብና የመሬት መጣበብ አደጋ ሊከሰት ይችላል በሚል ስጋት፣ የአንድ ልጅ የመውለድ መመሪያ ወይም (One child Policy))አውጥታ ነበር ።የኤኮኖሚው ሲያድግና ሲጠነክር ያንን መመሪያ በማንሳት የሁለት ልጆች ወሊድን ፈቅዳለች። በኢትዮጵያ ግን የመሬት ጥበት አያሰጋም፣አሁን ካለው ቁጥር እጥፍ ሊሸከም የሚችል መሬት አለ። ችግሩ ሕዝቡን የሚያስተናግድ መሬት ሳይሆን ሕዝባዊ ስርዓት የዘረጋው መዋቅራዊ ዝግጅትና የኤኮኖሚ ፖሊሲ አለመኖር ነው።አሁን ሕዝቡን ለችግር የዳረገውና ያጋለጠው ዋናው ነገር ዜጋ በአገሩ ሠርቶ ለማደር የማይችልበት፣ሰላምና አንድነቱን አጥቶ እርስ በራሱ እዬተጋደለ፣አንዱ አፈናቃይ ሌላው ተፈናቃይ የሆነበት ስርዓት መኖሩ ነው።

በጣም የሚያስቀው የአብይ አህመድ መንግሥት በርሃቡና በድርቁ ላይ ያወጣው መግለጫ ነው።ድርቅ የተፈጥሮ ውጤት መሆኑን አምኖ እርሃብ ግን በሰዎች ስንፍና የሚመጣ ክስተት ነው ብሏል።አባባሉን ሙሉ ለሙሉ የማንቃወመው ቢሆንም የእርሻ ፖሊሲውን ማን አበላሸው?ለእርሻው መስፋፋትና መሻሻል ትክረት ሳይሰጥ ማን በመናፈሻና በሕንጻ ግንባታ ላይ ተሰማርቶ ያገሪቱን ገንዘብ በተነ?ለአገር ውስጥ ፍጆታ ለሆነው በምግብ ላይ ሳይሆን ለውጭ ገበያ ለሚሆነው በአበባና በፍራፌሬ ምርት ላይ ማን ትኩረት ሰጥቶት ተሰማራ?ገበሬውን ማን አፈናቀለው?የመሬት ፖሊሲው ለገበሬው አመቺ ነወይ?ለገጠሩ ልማት መስፋፋት እንዳይችል ተጠያቂው ማን ነው?የሚሉትን ጥያቄዎች እንድናነሳ ያስገደደን መግለጫ ነው።በጥቅሉ ጥፋቱን በሕዝቡ ላይ የማላከክና እራሱን ነጻ የማድረግ ሙከራ ነው እንላለን።

ሌላው ትልቁ የአብይ አህመድ ክህደት በአሸባሪው ኦነግ ላይ የሰጠው ማብራሪያ ነው።ኦነግ ሸኔ እያለ በሚጠራው በመንግሥት ድጋፍ የሚንቀሳቀሰው ገዳይ ቡድን ስለሚፈጸመው ግድያ፣ዘረፋና ማፈናቀል ብዙም ሳይልበት አሸባሪውን ቡድን አንድ ጊዜ ዓላማ የሌለው፣ እዚህ ግባ የማይባል ተራ ሽፍታና ቀማኛ ነው ሲል መልሶ ይህንን ባለበት አፉ ከሕዝቡ ውስጥ የገባ፣የሕዝብ ድጋፍ ያለው በመሆኑ ለይቶ ለማውጣትና ለማሶገድ የሚያስቸግር ነው ሲል የቡድኑን ጥንካሬ በሚያጎላ መልኩ አቅርቦታል። በንጹሃን ላይ የሚያደርሰውን የጭፍጨፋ ወንጀል ሳይሆን በአንድ ድርጅትና ንብረት ላይ ያደረሰውን ጥቃት ከመኮነን ያለፈ የተናገረው አልነበረም።የእራሱን ድርጅት ኦሕዴድና ሌሎቹን ጨምሮ የኦሮሞ ሕዝብ እውቅናና ድጋፍ እንዳለው ሳያውቀው አጋልጧል።የኦነግም ሆነ የኦሕዴድ ወንጀል የኦሮሞን ሕዝብ የማይመለከተው ከሆነ በስሙ የሚነገድበት ሊቃወምና መልስ ሊሰጥበት ይገባል።ሌሎቹም

የኦሮሞ ልሂቃን እንደ መረራ ጉዴና አይነቶቹ ኦነግ የሁላችን፣እኛም የኦነግ አባላት ነን ሲል እቅጩን ተናግሯል።የአብይም ሆነ የመረራ መግለጫ በኦነግና በስርዓቱ ላይ ያለውን ብዥታ ስለሚያጠራው ለመወናበድ ዕድል አይሰጥም፣ለቆረጠ ሰው የትግል ምርጫውን አስተካክሎ እንዲሰለፍ ይረዳዋል እንላለን።አብይ አህመድ ተራ ሽፍታ ያለው አሸባሪ ቡድን ከተማ ይዞ ብዙ አሸባሪ እያሰለጠነ ፣ በድንኳን ድግስ ደግሶ የሚያስመርቅ ፣ የኮሚኖኬሽን መሥመር ዘርግቶ የተቀናጀ ጥቃት የሚፈጽም፣ ከባድ መሣሪያ ታጥቆ በኮንቮይ የሚንቀሳቀስ፣ከ400 ወረዳዎች በላይ ተቆጣጥሮ ግብርና ቀረጥ የሚሰበስብ ፣አስፋልት መንገድ ይዞ በፈለገበት አቅጣጫ እዬሄደ ሽብርና ዘረፋ የሚያካሂድ፣ የመንግሥትነት ሚና የሚጫወት ቡድን መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቀዋል።አብይ የማስታወስ ችግር ያለበት ሕዝብ ብሎ ቢፈርጀውም በዬእለቱ የሚኖርበትን ኑሮ የሚዘነጋው አይደለም።ችግሩ ተደራጅቶ ለጥቃቱ ተገቢ ምላሽ አለመስጠቱ ነው። እኛም ዘወትር ተደራጅ! እያልን የምንወተውተው ለዚያ ነው።አሁንም ደግመን ደጋግመን ተደራጅ እንላለን። በዚሁ የፓርላማው ውሎው አብይ አህመድ ያስተላለፈው ያልተጠበቀና አደገኛ ሃሳብ ደግሞ - የሚመጣውን የሙስሊም ኢድ በዓል አያይዞ ያቀረበው ጥሪ ነው።ምንም እንኳን የሙስሊም ኢትዮጵያውያን የኢድ በዓል በታላቅ ድምቀትና ክብር መከበር እንዳለበት ቢታመንም፣ የአብይ መንግሥት ጣልቃ ገብቶ እንደ ዲያስፖራው ክተት የገንዘብና የድጋፍ ማሰባሰቢያ ሰበብ ማድረጉ ብቻ ሳይሆን ለክርስቲያኑ በዓላት አከባበር ያላደረገውን ጥሪ ሲያደርግ በሁለቱ እምነት ተከታዮች መካከል አለመግባባት ከዛም ባለፈ ግጭት የሚጋብዝ ይሆናል። የሃይማኖት ነኩ ጉዳይ በእምነት ተቋማቱ ብቻ መፈጸም አለበት እንላለን።የሙስሊሙ ማህበረሰብ ከአብይ ሃሳብ ጀርባ ያለውን ተንኮል በቅጡ ሊመረምረው ይገባል።የሁለቱ እምነት ተከታዮች ተባብረውና ተከባብረው እንዳይኖሩ ማድረግ የስርዓቱ አንዱ መገለጫ ነው።ወያኔ ለኦርቶዶክስና ለሙስሊሙ ምዕመናንና እምነቶች ያሰበ መስሎ የትግራይና የኢትዮጵያ ብሎ ገነጣጥሎ ለማጥፋት የወሰደው እርምጃ በአብይ አህመድ መንግሥት በኩል በዚህ መልኩ ሲቀርብ ውጤቱ ግን አንድና ተመሳሳይ ነው።የእምነት ተቋማትን ማዳከም፣ምእመናንን ማጋጨትና በጠላትነት እንዲተያዩ ማድረግ አንዱ ኢትዮጵያን የማፍረሻ ስልት መሆኑን ሁሉም እስላሙም ሆነ ክርስቲያኑ ተገንዝበው በጋራ ወግድ ሊሉት ይገባል።

አብይ አህመድ ኢትዮጵያ አትፈርስም እያለ ኢትዮጵያን የሚያፈርስ ሕገመንግሥት መሸከሙን የዘነጋው ይመስላል።ያ ከሆነ ደግሞ የማስታወስ ችግር ያለበት እሱ እንጂ ሕዝቡ አይደለም።ያማ ባይሆን ኖሮ የተናገረውን የሚቃረን ንግግር በደቂቃዎች ልዩነት አያንጸባርቅም ነበር።

ያሳለፍነው ሰሞን የወያኔ ወረራና ግድያ በስፋት የቀጠለበት ፣በተለይም የአፋር ሕዝብ በተደጋጋሚ ለጥቃት የተጋለጠበት፣ብዙ ንጹሃን ሞተው፣ቆስለውና ከ300 ሽህ በላይ ተፈናቅሎበት የእርዳታ ያለህ ቢልም መንግሥት ነኝ ባዩ ጆሮ ዳባ ልበስ ብሎ የክህደት ተግባሩን በድጋሚ ያሳዬበት ሰሞን ነበር። የመከላከያ ተብዬውማ ባይነሳ ይሻላል።ጦርነቱ ተጠናቋል በማለት ጀነራሎቹ ካርታ ጨዋታ ላይ ተሰማርተዋል።የመንግሥት ግዴለሽነትና ዝምታ የአፋር ሕዝብ ኢትዮጵያዊ አይደለሁም ወይ ?የሚል ጥያቄ እንዲያነሳ አስገድዶታል።የኦነግ መራሹ ብልጽግና በኢትዮጵያዊነቱ የማይደራደረው የአፋር ሕዝብ እዚህ ህሳቤ ላይ እንዲደርስ የሚፈልገው በመሆኑ ደስተኛ ነው።ለሱ ችግሩ ኢትዮጵያዊ ነኝ ብሎ መቆሙ እንጂ በኢትዮጵያዊነቱ ላይ ጥያቄ ማንሳቱ አይደለም።

በአማራውም በኩል እንዲሁ ወያኔ የወሎን መሬት የራያንና አዘቦን እስከቆቦ አላማጣ ድረስ ተቆጣጥሮ ወልዲያን በቅርብ እርቀት ላይ ሆኖ በማሸበር ላይ እያለ ለነአብይ አህመድ መንግሥት ባለሥልጣኖች ችግራቸው አልሆነም፤እንዲያውም ለወያኔ ባለቤትነት እውቅና የሰጡ በሚመስል መልኩ ዝምታን መርጠዋል።በወልቃይትና ጠገዴም እንዲሁ የመደራደሪያ ካርታ ሆኖ ቀርቧል።የከባቢው አስተዳደር

አባላት አዲስ አበባ ተጠርተውም ይሁን በራሳቸው ፈቃድ መጥተው ስለከባቢው ችግር ከአብይ ጋር ለመነጋገር ጥያቄ ቢያቀርቡም ጊዜ የለኝም ብሎ ለምክትሉ ለደመቀ መኮንን አሳልፎ ሰጥቷቸዋል። በደመቀ መኮንን በኩል የተነገራቸውም የወልቃይትን ጉዳይ እንዲያለዝቡትና በሕዝበ-ውሳኔ እንዲፈታ ትብብር እንዲያደርጉ የሚጠይቅ ነበር።በኮሎኔል ደመቀ የሚመራው የወልቃይት አስተዳደር ግን የመጣነው የባንክ፣የሙብራት፣የውሃ፣የመገናኛ፣የአቅርቦት ችግር ስላለ የፌዴራል መንግሥቱን ለመጠዬቅ ነበር፤ግን መልስ አላገኘንም ብለዋል።በወልቃይትም ላይ በጉልበት ተነጥቀን የነበረውን በጉልበታችን መልሰነዋል።የምንደራደርበትና ለሕዝበ-ውሳኔ የሚወረወር አይደለም በማለት እቅጩን ተናግረዋል።ይህ እስከዬት ሊወስዳቸው እንደሚችል ወደፊት የሚታይ ይሆናል።የወያኔና የምዕራብ ዓለሙም ጥያቄ በሕገመንግሥቱ መሰረት በሕዝበ-ውሳኔ መልስ ያግኝ የሚል ነው።ሲወሩና ሲወስዱ በሕዝበ-ውሳኔ ያልሆነን መሬት አሁን በሕዝበ-ውሳኔ ይፈታ ብሎ ያንኑ ዝተት ሕገመንግሥት ጎትቶ ማምጣቱ ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም።የኦሕዴድ አነግ መራሹ ቡድን ይህንን ሕዝበ-ውሳኔና ሕገመንግሥት አገር ለማፍረስ  የሚጠቀምበት መሣሪያ ነው። ኢትዮጵያም በሕዝበ ውሳኔ አልተመሰረተችም፤በሕዝበ-ውሳኔም አትፈርስም።

አብይ አህመድ የሚመራው የብልጽግና መንግሥት ቀኝ እጁ በሆነው በአማራው ብልጽና  በኩል የአማራ ፋኖን ትግል ለማዳፈን ብዙ ጥረት አድርጓል።መሪዎቹን ለመግደል አለያም ለማፈን ተንቀሳቅሷል።ቅጥር ተላላኪዎችን በማሰማራት ዘረፋ በማካሄድ የፋኖን ስም ለማጠልሸት ሞክሯል። ለፋኖ መልካም አስተያዬትና ድጋፍ ያላቸውን የመንግሥት ተወካዮችንም በማስፈራራትና ከምድብ ስራቸው በማንሳት ለፋኖ ያለውን ፍርሃትና ጥላቻ አሳይቷል።በዚህ ውጥረት ውስጥ የሚገኘው ፋኖ ግን ደባውን እንዳመጣጡ እዬመለሰ ታጋዮችን በሚችለው መጠን እያሰለጠነ በማሰማራት ላይ ነው።ይህ ያስጨነቀው የባእዴን ተላላኪ ቡድን በፋኖ ላይ ከበባ አድርጎ የነበረ ሲሆን አይበገሬው ፋኖ ግን ከበባውን ሰብሮ ለመውጣት ችሏል።መንግሥት ተብዬው ቡድን ለበለጠ እርምጃ በመዘጋጀት ላይ መሆኑ ተሰምቷል፤ሕዝቡንም በማስፈራራት ከፋኖ ለመነጠል ሙከራ እያደረገ ይገኛል።የፋኖ ትግል አገር የማዳን ትግል ነው።የፋኖ ትግል በግፍ የሚጨፈጨፈውን ሕዝብ በተለይም አማራውን ለማዳን ነው።ስለሆነም ኢትዮጵያን አድናለሁ የሚል ሁሉ ከፋኖ ጎን ሊሰለፍ ይገባል።የቻለ በመቀላቀል ያልቻለ በስንቅና ትጥቅ ብሎም በፕሮፓጋንዳው መስክ ተሰልፎ የድርሻውን መወጣት ይጠበቅበታል።የአሁኗ ኢትዮጵያ ለመኖር የበቃችው አያት ቅድመአያቶቻችን ባደረጉት የፋኖ ሕዝባዊ ትግል ነው።ፋኖ ሌባና አሸባሪ አይደለም።ፋኖ የሌባ መድሃኒት፣የዘረኞችና ያሸባሪዎች፣የወራሪዎችም  ጸር ነው።

የመንግሥት ሴራ በፋኖ ላይ ብቻ አላቆመም።በአማራው ልዩ ሃይልም ላይ የብተናና የማዳከም እርምጃውን በስፋት ተያይዞታል።የበላይ አዛዥ የሆነውን ብርጋዴር ጀነራል ተፈራ ማሞን  በመሻር ለማፍረሱ ተባባሪ ይሆናል ያለውን ጀነራል ሾሟል።የኦሮሞ ክልል በሥልጣን ላይ ባለው መንግሥት እገዛ በሙቶ ሽዎች የልዩ ሃይል ጦር ሲያዘጋጁ ምንም ያላለው መንግሥት በአማራው ላይ መዝመቱ ላቀደው አገር የመበተን ዓላማው እንቅፋት ይሆነኛል በሚል ፍርሃት መሆኑ ግልጽ ነው።የልዩ ሃይሉም አዛዥ ጄነራል ተፈራ ማሞ በግልጽ የተናገረው ሃቅ ይኸው ነው።

የሰላምና የምክክር ኮሚሽን ተብሎ የተቋቋመው አካል ሥራውን ሳይጀምር በመፈራረስ አዝማሚያ ላይ ይገኛል።በተመደቡት ሰዎች አመራረጥ ላይ የተነሳው ጥያቄ መልስ ሳያገኝ፣ በመሪነት የተሰዬሙት ዶር አርአያ  መንግሥት በሥራዬ ጣልቃ የሚገባ ከሆነ እለቃለሁ የሚል ቃል አሰምተዋል።ለዚህ አባባላቸው ምክንያት ሊሆን የሚችለው መንግሥት የሚፈልገውን ለማስፈጸም የሚያደርገው ጣልቃ ገብነት መኖሩ ነው። በሌላም በኩል የስርዓቱ  ደጋፊና አካል የሆነው ኢዜማ የተባለው ድርጅት ስለኮሚሽኑ ባወጣው

መግለጫ ኮሚሽኑ በተንኮል የተተበተበና ግልጽነት የሌለው በመሆኑ የኢትዮጵያን ችግር ሊፈታ አይችልም ሲል ተቃውሞ አሰምቷል።

የዩክሬንና የሩስያ ጦርነት በኢትዮጵያ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽእኖ

ኢትዮጵያ የሁለቱም አገሮች ወዳጅ ስትሆን የዲፕሎማሲ ግንኙነትም አላት።ከሁለቱም ጋር የንግድ ልውውጥ ታደርጋለች።ቡና፣ፍራፍሬና አበባ ልካ ከዩክሬን ስንዴ፣እንቁላልና ዘይት ከራሽያም ስንዴ ዘይትና የቴክኖሎጂ ውጤቶች በተለይም የጦር መሣሪያ ታገኛለች።በቅርቡም ሰፋ ና ጠንከር ያለ ስምምነት ተፈራርማለች።ጦርነቱ ከቀጠለ ይኸ ሁሉ ይቋረጣል ወይም ዋጋው ይወደዳል ማለት ነው። ገና በጅምሩ በኡክሬን ውስጥ ለትምህርትና ለንግድ ሥራ የሄዱት ኢትዮጵያውያኖች ህይወታቸውን ለማትረፍ በፖላንድ በኩል ወደ ጀርመን መግባታቸው ተሰምቷል።

የዓለም አገሮች ሰልፋቸውን ከአንዱ ጋር በማድረግ ላይ ናቸው፤ከሁለቱም ጋር ለማድረግ የሚቻልበት ሁኔታ የለም።በአሜሪካን የሚመራው የምዕራቡ ዓለም ከዩክሬን ጎን ሲሰለፍ አሜሪካንን የሚቃወመው ደግሞ ከሩስያ ጎን ተሰልፏል።ግልጽም ባይሆን  ቻይና፣ሰሜን ኮሪያ፣ኢራን፣ሕንድና ፓኪስታን፣ከሩስያ ጎን እንደሚሰለፉ ምልክቶች እዬታዩ ነው።የደቡብ አሜሪካ አገሮችም እንዲሁ።የብራዚሉን መሪ ቦልሳናሮን የአሜሪካው መሪ ባይደን ደውሎ ምነው ዝም አልክ ቢለው እባክህ ሞኝህን ፈልግ ማለቱ ተሰምቷል።አዎ በሩስያ ላይ መጠነ ሰፊ የኤኮኖሞ፣ እቀባ ቢጣልም ቀደም ሲል ባደራጀችው የብሪክስ(BRICS) ውህደት፣የብራዚል፣ራሽያ፣የሕንድ፣የቻይናና የደቡብ አፍሪካ ግንባር ልትቋቋመው የምትችልበት ጉልበት ይኖራታል። ግብይቷንም በነሱ በኩል ማድረጓ አይቀርም።የአፍሪካ አገሮች በሰፌድ ላይ የሚዋልል ውሃ ሆነዋል።ሕዝባቸው ለአሜሪካና ለአውሮፓውያን ያለው ስሜት እምብዛም ነው።በገንዘብ ተሰበው ከአሜሪካኖች ጎን ቢሰለፉ ከሕዝባቸው ጋር መቀያየም ይሆናል፤ ብቻ አይተነው ጊዜ ወደሚያዋጣው የሚል አቋም የያዙ ይመስላል።ኢትዮጵያም ብትሆን ከዚህ የተለዬ አቋም የያዘች አይመስልም። ለኢትዮጵያና ለመሰሎቿ የሞተው ወንድምሽ የገደለው ባልሽ፣ሃዘንሽ ቅጥ አጣ ከቤትሽም አልወጣ ሆኖባቸዋል።

ይህ ጦርነት በፍጥነት ካልቆመ ከፍ ወዳለ ደረጃ ብሎም ወደ ሚፈራው የሦስተኛ ዓለም ጦርነት ያመራል ተብሎ ተፈርቷል።ሁለቱ የዓለም ጦርነቶች በዛው የባልካን አገሮች ውስጥ ስለተጀመረ ይህም በዛው አካባቢ መሆኑ ለስጋቱ የታሪክ ተያያዥነቱ መነሻ ይሆናል።ዓለም በውጥረትና በችግር ፣በኑሮ ውድነትና በግጭት ሰላም ባጣችበት በዚህ ወቅት ሁሉም የብሶቱንና የፍላጎቱን መውጫ ሊያደርገው እንደሚችል ብዙ ይባላል። በቀውስ ውስጥ የሚዳክር አገር ከገጠመው ተቃውሞ ለማምለጥ ከጎረቤት አገር ጋር ጦርነት መጫሩ የተለመደ ነው።ይህ ጦርነት ግን የተለዬ ነው፤የግዛት አንድነት ጥያቄ ምክንያት ያደረገ ነው።አሜሪካኖች ሩስያን የሚያዳክሙ መስሏቸው በአጠገብ የሚገኙትን አገራት ጠብ ቆስቋሽ ለማድረግ ብዙ ሲጥሩ ቆይተዋል።ለዚያ ፍላጎታቸው የተመቸችና ታዛዥ ሆና የተገኘችው ኡክሬን ናት። ብዙ የተsfa ዳቦ እያሳዩ ከማትችለውና ከማትወጣው ፈ,ና eስጥ እንድትገባ አድርገዋታል።አቅሟን ያላወቀችው ኢክሬን ለዘመናት አብራ ከኖረችው ጎረቤት አገር፣kmዚያም ባለፈ የሕዝቧ እሩብ የሚሆነው ሩሲያዊ ሆኖ ሳ| የአሜሪካnna የምዕራባውያን የጥፋት መልእክተ።ኛ ሆኖ ለጥቃት መጋለጥ የሚያሳፍር ነው።አሜሪካኖችና ምዕራባውያን የሌላውን አገር ቀስቅሰው ካተራመሱና ካፈራረሱ በኋላ ጣጥለው እንደሚሄዱ ታሪካቸው ይመሰክራል፣፣በኢራቅ፣በሊቢያ፣በሶሪያ፣በአፍጋኒስታን---ወዘተ የፈጸሙት በቂ ማስረጃ ነው።አሁንም ኡክሬንን ለመታደግ ጦርነት ውስጥ አንገባም በምንሰጥሽ መሳሪያ እራስሽ ተወጭው የሚል አስደንጋጭ መርዶ ተነግሯት ያገሪቱ መሪ ዘለንስኪ ጉድ አደረጋችሁን እያለ በአደባባይ ሙሾ እያወረደ ነው።ሕዝቡም እግሩ እንደመራው በጎረቤት አገራት እዬተሰደደ ነው። አሜሪካኖቹም ሆኑ አጫፋሪ የአውሮፓ አገራት የኡክሬን ልዑላዊነትና ዴሞክራሲ ተደፈረ የሚል

ጫጫታ ከማሰማት ያለፈ ሩስያን ለመውጋት አይደፍሩም።የሩስያ ነዳጅና ጋዝ ጥገኛ የሆኑትም ግራ ተጋብተው የሚያደርጉት ጠፍቷቸዋል።እንደው በየአዳራሹ የኡክሬንን ባንዲራ ይዘው ከመሰለፍ በቀር ለኡክሬናውያን ችግር ዘላቂ መፍትሔ ለማምጣት አለመቻላቸው ታይቷል።በዚህ የተማመነው ቪላድሚር ፑቲን ሌላ ነገር ብታስቡ ጉድ ይፈላል እያለ እያስቦካቸው ነው።የኡክሬን ከተማ ኪዬቭ በቀናት ውስጥ ሙሉ ለሙሉ በሩስያ ወታደሮች ቁጥጥር ስር እንደምትውል ከሂደቱ እዬተነገረ ነው። ሌሎቹም የአሜሪካ አምላኪ የከባቢው አገራት የወደፊቱን የፖለቲካ አሰላለፋቸውን ሊቀይሩ ይችላሉ የሚለው የምዕራባውያን ስጋት እያደገ በመሄድ ላይ ነው።

ምዕራባውያን የሌላው አገር ልዑላዊነት ሲደፈር እነሱም ሲደፍሩ ግን ቅር አይላቸውም።ሱዳን የኢትዮጵያን መሬት ወራ ስትይዝ፣ወያኔ ከግብረአበሮቹ ጋር ለዑላዊት አገር ለማፍረስ አላይና እታች ሲል ከጎኑ ቆመው ከመደገፍ ሌላ መቼ ለኢትዮጵያና ለሕዝቧ አሰቡ?የነሱ ዴሞክራሲና ልዑላዊነት ማለት በአውሮፓ ድንበር ውስጥ የተከለለ እንጂ በሌላው የአፍሪካ፣የደቡብ አሜሪካ፣የእስያና የመካከለኛው ምስራቅ አገራት አይደለም።

የሚፈራው ነገር ጦርነቱ ከቀጠለና ሩስያ ኡክሬንን በጉልበት ካንበረከከች፣ቻይና ታይዋንን፣ሰሜን ኮሪያ ደቡብ ኮሪያን፣ለመያዝና የግዛት አንድነታቸውን ህልም ተግባራዊ ከማድረግ የሚያግዳቸው ሃይል አይኖርም።ሕንድና ፓኪስታንም በካሽሚር ምክንያት የለዬለት ጦርነት ከማካሄድ ወደ ኋላ አይሉም። በአፍሪካም ሆነ በደቡብ አሜሪካና በመካከለኛው ምስራቅ እንዲሁ በድንበር የሚነታረኩት አገራት ከጦርነት ሰልፍ ውስጥ መግባታቸው አይቀሬ ይሆናል፣የሦስተኛው ዓለም ጦርነት ማለትም ይኸው ነው።

ኢትዮጵያስ የተወሰደባትን መሬቷን ለማስመለስ ከወሳጁ ጋር ጦርነት ትገጥም ይሆን?ወያኔንስ ለማንበርከክ መቀሌ ድረስ ለመግባት ዕድሉን ትጠቀምበት ይሆን?አንዳንድ የፖለቲካ ተንታኞች ምዕራብ ዓለሙ በኡክሪን ላይ በማተኮሩ ለወያኔ ይሰጥ የነበረው ድጋፍ ቀዝቀዟል፤የአብይ መንግሥት ወያኔን የምሩን ቢያቀምሰው ለምን ብሎ የሚጠይቀው አይኖርም ይላሉ።በእኛ ግምት ግን የአብይ አነጋዊ መንግሥት የወለደውን ወያኔን ለማጥቃት ፍላጎትም ሆነ ድፍረቱ የለውም የሚል ነው።

ለማንኛውም ሳይቃጠል በቅጠል ብሎ ጦርነቱ የሚቆምበትን መንገድ መሻቱ ለሁሉም መልካም ነው። ለኡክሬን ከአትላንቲክስ ወዲያ ማዶ እርቀ ካለው አሜሪካ ይልቅ በታሪክ፣በባህልና በቋንቋ እንዲሁም በመልካም ጉርብትና ከኖረችው ከሩስያ ጋር በሰላም ብትኖር የሚጠቅማት ይሆናል።አሁንም ሕዝቧ እዬሸሸ የሄደው ወደ ጎረቤት አገሮች እንጂ ወደ አሜሪካ አይደለም።

የጦርነት ሁሉ ምክንያቱ ጥቅም ነው።የሃይማኖትም ሆነ የጎሳ ከፍ ሲልም የአገራት ግጭትና ጦርነት ፣ መነሻው የእኔ ከሚለው እራስ ወዳድነት የተነሳ ነው።ጦርነት መጨረሻ የለውም፣እያንዳንዱ ጦርነት ሲቆም በማህጸኑ ውስጥ ቀጣዩን ጦርነት አርግዞ ነው።የሰው ልጅ ታሪክ የጦርነት ታሪክ ነው።ከጦርነት ያልተለዬ ስለሆነ አንዱን ጦርነት ሲጨርስ ለሌላው ጦርነት ዝግጅት ያደርጋል።መሣሪያው እንጂ አስተሳሰቡ አልተቀየረም።ከድንጋይ ወደ ጦር፣ወደቀስትና ጠመንጃ፣ሚሳይልና ሮኬት፣ኑክሌርና አሁን ደግሞ በሳይበር ቴክኒዎሎጂ ጥቃት ማንበርከክ ከሚቻልበት ደረጃ ላይ ተደርሷል።የወደፊቱስ ምን ይሆን?

ዓለማችን ከተደቀነባት የጦርነት አደጋ ትወጣ ዘንድ ምኞታችን ነው።ሰላም ለዓለም ሕዝቦች ይሁን!!

ኢትዮጵያ በአንድነትና በነጻነት ለዘለዓለም ትኑር!!